# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከማርች 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እና ከማርች 21-31/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ማርች 2022
አዲስ አበባ

**ርዕስ** **ገፅ**

እ.ኤ.አ ከማርች 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ ....3

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20 /2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....4

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20 /2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ....5

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20 /2022 ድረስ የነበረው የዝና ብመጠን ....6

ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ....6

እ.ኤ.አ ከማርች 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....7

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....7

እ.ኤ.አ ከማርች 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....8

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....8

እ.ኤ.አ ከማርች 21-31/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ ....9

እ.ኤ.አ ከማርች 21-31/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....10

እ.ኤ.አ ከማርች 21-31/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....10

# ኢ.ኤ.አ ከማርች 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ


በማርች ሁለተኛው አሥር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ደረቅ፣ ፀሐያማና ሞቃታማ የአየር ሁኔታ ተስተውሏል። ይሁንና የበልግ ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች በአንፃራዊ መልኩ ከመጠናከራቸው ጋር ተያይዞ የተሻለ የደመና ሽፋን በመስተዋሉ የደቡብ ምዕራብ፣ የመካከለኛውና የሰሜን የሀገሪቱ ክፍሎች ዝናብ ነበራቸው። በመሆኑም ምዕራብ፣ ኦሮሚያ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ምዕራባዊ ክፍል፣ በምሥራቅ፣ በመካከለኛውና በደቡብ አማራ በጥቂት ቦታዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ አግኝተዋል። ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከመዘገቡ ጣቢያዎች መካከል በአምባ ማርያም 46.4፣ በማሻ 30.4፣ በሻምቡ 44.3፣ በወሊሶ 32.3 እንዲሁም በአማን 33.8 ሚ.ሜትር የደረሰ ከባድ ዝናብ ተመዝግቧል።

በዚሁ መሠረት ቀደም ሲል መደበኛውን ፊር ተከትሎ መዝነብ ከሚገባው የበልግ ዝናብ መዘግየት ጋር ተያይዞ ተፈጥሮ የነበረውን ደረቅ ሁኔታ ሊያረግብ የሚችልና በከባቢ አየር ውስጥ የእርጥበት መጠን መጨመሩ በቀጣይነት ለሚፈጠሩት ዝናብ ሰጪ ክስተቶች መጠናከር ምቹ ሁኔታን እንደፈጠረ መገመት ይቻላል። በሌላ በኩል በአቦቦ፣ በጋምቤላ፣ በላሬና በመተማ አካባቢዎች ላይ ከ40 ዲግሪ ሲልሽየስ በላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ተመዝግቦባቸዋል።


ባለፉት አሥር ቀናት የዘነበው ዝናበ ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም ከ5-75 ሚ.ሜ. ዝናብ ከአማራ ደቡብና ሰሜን ጎንደርና ወሎ፤ አብዛኛው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፤ ከኦሮሚያ ኢሉአባቦራ፣ ጂማ፣ የባሌ ደቡባዊው ክፍልና ሁሉም የሸዋ ዞኖች ከጋምቤላ የመዠንግ እንዲሁም አዲስ አበባ ከ2-7 ቀናት ያህል አግኝተዋል (ካርታ 1 እና 2) ።

ባለፉት አሥር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን በአማካይ ከሚጠበቀው ጋር ሲነጻጸር ከአማራ ደቡብና ሰሜን ጎንደርና ወሎ፤ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የደቡብ ኦሞ እና የቤንች ማጂ፤ ከኦሮሚያ ኢሉአባቦራ፣ ጂማ፣ አብዛኛው የሸዋ ዞኖች፤ ከጋምቤላ የመዠንግ እንዲሁም አዲስ አበባ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናበ የነበራቸው ሲሆን፤ የቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች ከመደበኛው በታች ዝናበ እንደነበራቸው መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 3) ።


ካርታ 1   እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20 /2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2     እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20 /2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20 /2022 ድረስ የነበረው የዝና ብመጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር







ከመደበኛ በታች መደበኛ ከመደበኛ በላይ

## እ.ኤ.አ ከማርች 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍናቸው የማርች ወር ሁለተኛው አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ አመዝኖ ተስተወሏል፡፡ ይሁን እንጂ በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን በመስተዋሉ በምዕራብ፣ በኦሮሚያ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ምዕራባዊ ክፍል፣ በምሥራቅ፣ በመካከለኛውና በደቡብ አማራ በጥቂት ቦታዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ አግኝተዋል። ይህም ሁኔታ በተለይም የበልግ ሰብል አብቃይ በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የበልግ ዝናብ መዘግየት ጋር ተያይዞ ተፈጥሮ የነበረውን የዘር ወቅት አስቀድሞ ለመጀመር አዳጋቸ የነበረውን ሁኔታ በተወሰነ ደረጃ እንዲሻሻል በማድረጉ አርሶ አደሮች የማሳ ዝግጅት ለማድርግ እና የተለያዩ ሰብሎችን ለመዝራት አዎንታዊ ሚና የነበረው ሲሆን አስቀድመው ለተዘሩ የበልግ ወቅት ሰብሎችም ሆነ በአካባቢዎቹ ለሚበቅሉ ቋሚ ተክሎች እንዲሁም ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት በጎ ሚና ነበረው። በተጨማሪም ከከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ የተገኘው ከፍተኛ መጠን ያለው እርጥበት በተለይም ውኃ አጠር ለሆኑት አካባቢዎች የዝናብ ውኃን ለማሰባሰብና ለማከማቸት የሚያስችል ነበረ (ካርታ 4)፡፡


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከማርች 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፈው የማርች የሁለተኛው አስር ቀናት የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ ስንመለከት በአብዛኛው በላይኛውና በመካከለኛው አባይ፣ በባሮ አኮቦ፣ በአብዛኛው ኦሞ ጊቤ፣ በጥቂት የላይኛው አዋሽ እና ስምጥ ሸለቆ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ እንደነበረ ተስተውሏል፡፡ በተጨማሪም በመካከለኛው ኦሞ ጊቤ እንዲሁም በላይኛው አባይ እና ባሮ አኮቦ ተፋሰሶች ላይ ከፍተኛ እርጥበት እንደነበራቸው ያሳያል። በሌላ በኩል የተቀሩት ተፋሰሶች ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ ስር ነበሩ (ካርታ 5) ፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




# እ.ኤ.አ ከማርች 21-31/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ


በመደበኛ ሁኔታ የበልግ ዝናብ እየተስፋፋና እየተጠናከረ የሚሄደው ከማርች አጋማሽ በኃላ ነው፡፡ በመሆኑም በማርች ሶስተኛው አሥር ቀናት አብዛኛዎቹን የበልግ አብቃይና ተጠቃሚ ቦታዎችን ባካተተ መልክ በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሻለ ዝናብ ይስተዋልባቸዋል፡፡

በሚቀጥሉት አሥራ አንድ ቀናት በተለይም በደቡብ፣ በመካከለኛዉና እና በደቡብ ምሥራቅ ቦታዎች ላይ ዝናብ ሰጭ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለይም በመጀመሪያዎቹ የሳምንቱ ቀናት ላይ አንጻራዊ የሆነ ጥንካሬ ሊኖራቸው እንደሚችል የተለያዩ የትንበያ መረጃዎቻችን ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያይዘ በአብዛኛው የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት በደቡብ ብ/ብ/ህዝቦች፣ በሲዳማ፣ በምስራቅ አማራ፤ በኦሮሚያ እና በሶማሌ በተለያየ ሥፍራዎቻቸዉ ላይ ዝናብ ሊያገኙ እንደሚችሉ ይጠበቃል፡፡

በአጠቃላይ  ከኦሮሚያ ክልል ጅማ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ አርሲ፣ ባሌ፣ ቦረናና ጉጂ፣ ምዕራብ ሐረርጌ፣ አዲስ አበባ፤ ከአማራ ክልል ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ እንዲሁም ሰሜን ሸዋ፣ የምሥራቅና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፤ ሁሉም የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች ህዝቦች እንዲሁም የሲዳማ ክልል፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ  ደግሞ የከፋና የቤንች ማጂ ዞኖች፤ ከሶማሌ ክልል የሊበን እና አፍዴራ ዞኖች፤ የሐረሪና የድሬዳዋ አካባቢዎች  ከቀላል እስከ ከመካከለኛ  እንዲሁም በጥቂት ስፍራዎቻቸው ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ሊያገኙ እንደሚችሉ ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም የምሥራቅ አማራ አጎራባች የሆኑት የደቡብ ጎንደር፣ የምሥራቅ ጎጃም፤እንዲሁም የአፋር ክልል ዞን 3 እና 5  በጥቂት ሥፍራዎቻቸው ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች በአመዛኙ ደረቅ ሆነው ይሰነብታሉ።




እ.ኤ.አ. ከማርች 21-31, 2022 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ.




እ.ኤ.አ. ከማርች 21-31, 2022 የሚኖረዉ የቀኑ ከፍተኛ የአየር ሙቀት መጠን በዲ.ሴ

## ኢ.ኤ.አ ከማርች 21-31/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ ከማርች አጋማሽ በኋላ የበልግ አብቃይ እና የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ አካባቢዎች ላይ የእርጥበት ሁኔታው አንጻራዊ በሆነ መልኩ በመጠንም ሆነ በሽፋን የሚስፋፋበት በመሆኑ የበልግም ሆነ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች በሰፋት የሚዘሩበት ወቅት ነው።

በተሰጠው የአየር ሁኔታ ትንበያ መሰረት በሚቀጥሉት የማርች ሶስተኛው አስር ቀናት አብዛኛውዎቹ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚና ሰብል አምራች አካባቢዎች ላይ የወቅቱ እርጥበት ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ እንደሚሄድ ይጠበቃል። በተለይም በደቡብ፣ በመካከለኛውና በደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ አንጻራዊ የሆነ ጥንካሬ ሊኖራቸው እንደሚችልና ከቀላ እስከ ከባደ መጠን ያለው ዝናብ ሊያገኙ እንደሚችሉ በትንበያው ላይ ተመልክቷል። ይህም ሁኔታ የማሳ ዝግጅት ለማድርግ እና የተለያዩ ያጭርና የረጅም ጊዜ የበልግም ሆነ የመኸር ወቅት ሰብሎችን ለመዝራት አዎንታዊ ሚና የሚኖረው ሲሆን አስቀድመው ለተዘሩ የተለያዩ የበልግ ወቅት ሰብሎች እንዲሁም ለቋሚ ተክሎችና ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት በጎ ሚና እንደሚኖረው ይጠበቃል። በመሆኑም በተለያዩ ምክንያቶቸ ዘር ለመዝራት የዘገዩ አካባቢዎቸ የሚጠበቀውን የእርጥበት መሻሻል ከግምት በማስገባት በቂ ዝግጅት ከወዲሁ እንዲያደርጉ ይመከራሉ። በተጨማሪም እርጥበት አጠር የሆኑ አካባቢዎች ላይ የሚኖሩ አርሶ አደሮችም ሆኑ አርብቶ አደሮች በመካከል ለሚከሰቱ ደረቅ ሰሞናት ጥቅም ላይ ማዋል የሚያስችል የዝናብ ውኃ የማሰባሰብና የማከማቸት ተግባራትን ለማከናወን ከወዲሁ አስፈላጊውን ዝግጅት እንዲያደርጉ ይመከራሉ።

## ኢ.ኤ.አ ከማርች 21-31/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስራ አንድ ቀናት ለዝናብ መኖር መንስኤ የሚሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ቀስ በቀስ እየተጠናከሩ ሊሄዱ እንደሚችሉና ከዚሁ ጋር ተያይዞም በተለይም በመጪዎቹ ጥቂት ቀናት በአንዳንድ የደቡብ፣ የመካከለኛዉ እና የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ተፋሰሶች  ላይ የተለያየ የእርጥበት መጠን ሊኖራቸዉ እንደሚችል የትንብያ መረጃዎቻችን ያመለክታሉ፡፡ ከነዚህም ተፋሰሶች የላይኛዉ ባሮአኮቦ፣ አዋሽ፣ በጥቂት የላይኛዉና የመካከለኛዉ አባይ፣ በአብዛኛው ኦሞጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ገናሌ ዳዋ እንዲሁም በጥቂት የላይኛዉ ዋቢ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ ሊያገኙ እንደሚችል የሚጠበቅ ሲሆን፤ የተቀሩት አብዛኛዎቹ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ እና ከፊል ደረቅ የአየር ሁኔታ ሊኖራቸው እንደሚችል ይጠበቃል፡፡